# የቢዝነስ ፕላን (እቅድ) ዝግጅት

(ከአማራ ክልል የቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ የተገኘ)

## የቢዝነስ ፕላን (እቅድ) ምን ማለት ነው?

- ማንኛውም አንተርፕራይዝ ሊተገብር ያሰበው የንግድ ስራ ግብና ዓላማ ምን እንደሆነ፣ የስራው ሂደት ምን እንደሚመስልና እንዴት እንደሚሠራ እንዲሁም እያንዳንዱ ክንውን መቼ እንደሚሰራ የሚያስረዳ ዶኩመንት (ሰነድ) ነው፡፡
- የታለመውን ግብ ለመምታት የሚያስችል የአሰራር መመሪያን የያዘ ነው፡፡
- የኢንተርፕራይዙን  የቢዝነስ /የንግድ ስራ አሰራር ፍኖተ ካርታ ያሳያል፡፡
- የኢንተርፕራይዙን የቢዝነስ/የንግድ ስራ  ያለውን እድል ለገንዘብ ተቋማትና ባለሀብቶች ሊያስረዳ የሚችል ሰነድ  ነው፡፡
- የኢንተርፕራይዙን የቢዝነስ/የንግድ ስራ ሊኖረው የሚችለውን ማንኛውንም እድል /ሁኔታ በመዘርዝር የሚታቀድበት በቂ ቅድመ ዝግጅት የሚደረግበት ነው፡፡

## የቢዝነስ / የንግድ ስራ ፕላን (እቅድ) ለምን ይዘጋጃል?

- የቢዝነስ / የንግድ ስራ ፕላን (እቅድ) በተዘጋጀው ግብና ዓላማ ላይ ትኩረት / አጽንኦት በመስጠት ስራን ለማከናወን ይረዳል፡፡
- የገንዘብ አቅምን ከተለያየ ምንጭ ለማግኘት ይረዳል፡፡
- ቢዝነሱ/የንግድ ስራው የሚጀመርበትንና ሊመራበት የሚገባውን ስርዓት በማሳየት አቅጣጫ ጠቋሚ ይሆናል፡፡
- በተነደፈው የቢዝነስ /የንግድ ስራ ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት ካላቸው አጋር ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ይረዳል፡፡
- የተነደፈው የቢዝነስ /የንግድ ስራ የስኬት እድል ያለው መሆኑን ለማሳየት ይጠቅማል፡፡
- በኢንተርፕራይዙ ውስጥ ቢዝነሱን /የንግድ ስራውን ለማስተዳደር የሚያስፈልገው በቂ ችሎታ እንዳለ መኖሩንና ለሚመረተው ምርትና አገልግሎት የገበያ እድል መኖሩን ለማረጋገጥ ይጠቅማል፡፡
- ስራው ከተጀመረ በኃላ በጊዜ ሂደት ውስጥ በእቅድ ደረጃ የተቀመጠውን ውጤት በተግባር ከሚሆነው ጋር ለማወዳደር ይረዳል፡፡

## የቢዝነስ / የንግድ ስራ ፕላን (እቅድ) እንዴት ይዘጋጃል?

- በቢዝነስ / በንግድ ስራ ውስጥ የሚጠየቁ ማንኛውንም ጥያቄዎች በመዘርዘርና ለጥያቄዎቹ  መልስ በመስጠት
- ከተጠየቁት / ሊጠየቁ ከሚችሉት ጥያቄዎች መካከል ምላሽ ለመስጠት ተጨማሪ መረጃ በማሰባሰብ
- አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በሙሉ በማሰባሰብ
- የተለያዩ አማራጮችን በማወዳደርና የተሻለውን አማራጭ ለመውሰድ በመወሰን

## በቢዝነስ ፕላን (እቅድ) ምን ሊደረግ ይችላል

- የቢዝነስ/ የንግድ ስራ ፕላን (እቅድ) አስቀድሞ ማዘጋጀት ለክትትል ይረዳል፡፡ ይህም ማለት በእቅድ የተያዘውን ስራ ከተከናወነው ስራ ጋር በማነጻጸር ለመገምገም ይጠቅማል፡፡
- ከገንዘብ ተቋማት እንዲሁም ፍላጎት ካላቸው አጋር ድርጅቶች ጋር ለሚደረግ ውይይት የመነሻ ሃሳብ ይሆናል፡፡

- የቢዝነስ / የንግድ ስራ እቅድ ለጅምላ ንግድ፣ ለችርቻሮ ንግድ፣ አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ድርጀት፣ ምርት የሚያመርት (አምራች) ድርጅት፣ ማንኛውም የንግድ ድርጅት፣ ለገንዘብ ተቋማትና ለንግድ ዘርፍ ባለቤቶችና ስራ አስኪያጆች ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

**የቢዝነስ ፕላን (እቅድ) ገጽታ ምን ይመስላል?**

- የተተየበና በጥራዝ የተቀመጠ፣ በንጽህና የተጠበቀ/የተያዘ፣ ማጠቃለያና እዝል ያለው (ዋናውን እቅድ ላለማስረዘም ማለት ነው)፣ እያንዳንዱ ገጽ የገጽ ቁጥር የተሰጠው፣ በሚመለከተው አባል የተፈረመ መሆን የተገባው ሲሆን የቢዝነስ እቅድ መድብል ብዙ ወይም ጥቂት መሆን የሚወሰነው እንደ ንግዱ የዘርፍ ዓይነት ነው፡፡

**የቢዝነስ / የንግድ ስራ ፕላን (እቅድ) ማንን ያካትታል?**

- የንግድ ዘርፉ ተጠቃሚ የሆኑ ደንበኞችን፣ በዘርፉ የሚሰሩ ተወዳዳሪ ግለሰቦችና ድርጅቶች፣ አቅራቢዎች፣ ተቀጣሪዎች፣ ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶች፣ የንግድ ስራው የሚካሄድበት ስፍራ ወይም አድራሻ፣ ለንግዱ ስራ የሚያስፈልገው ቁሳቁስ. ወዘተ

**የቢዝነስ ፕላን (እቅድ) ፎርማት**

- **ስለንግድ ስራው አጭር መግለጫ**
- **የኢንተርፕራይዙ ስም**
- **ኢንተርፕራይዙ በሕግ የሚኖረው የሰውነት ዓይነት**

ሀ/ በአንድ ሰው ባለቤትነት ለ/ በአጋርነት የሚሰራ ሐ/ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር መ/ ኮርፖሬሽን

**ይህ ሕጋዊ ሰውነት የተመረጠበት ምክንያት**

**የተጠሪ አድራሻ**

ስልክ ቁጥር ______________

ኢሜይል ______________

ፋክስ ______________

**የንግድ ስራ ዓይነት**

አምራች ______________ አገልግሎት ሰጪ ______________

ጅምላ ሻጭ ______________ ችርቻሮ ንግድ ______________

**ኢንተርፕራይዙ ስለሚሰራው የቢዝነስ/ ንግድ ስራ አጭር ዘገባ**

- የሚያመርተው የምርት ዓይነት እና የሚሰጠው አገልግሎት

- ገበያን በተመለከተ ኢንተርፕራይዙ ትኩረት የሚሰጠው የህብረተሰብ ክፍል ወይም ተቋም

- ቢዝነሱ / ንግዱ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተው አስተዋጽኦ

- የኢንተርፕራይዙ መስራቾች / አባላት ግለታሪክ መግለጫ

| ተራ ቁጥር | ስም ከነአያት | አድራሻ | የትምህርት ደረጃ | በኢንተርፕራይዙ ውስጥ ያለው የሥራ ኃላፊነት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |

**1. ገበያ ነክ እቅድ**

- ኢንተርፕራይዙ ምርቱን ስለሚያቀርብበት / ስለሚሸጥበት ገበያ ማብራሪያ (ገበያው የሚገኝበት አካባቢ፣ ታሳቢ የሚደረጉት የደንበኞች ዓይነት፣ ጠቅላላ የገበያ ሽፋን፣ ተወዳዳሪ አምራቾች ካሉ ስለሚያቀርቡት ምርትና አገልግሎት አጭር ማብራረያ፣ ተመሳሳይ ምርትና አገልግሎት የሚቀርብ ከሆነ በገበያው ውስጥ ስለሚኖረው ድርሻና የመሳሰሉት ይገለጽ)
- ምርቱ /አገልግሎቱ በገበያ ውስጥ የሚኖረው ድርሻ (ምርቱን ለማምረትም ሆነ ለመሸጥ የሚያስፈልጉት ግብዓቶች)
- ኢንተርፕራይዙ የሚያቀርበው ምርት በአካባቢው ካሉ ሌሎች ተመሳሳይ አምራቾች የሚለይበትና ገበያውን ወደራሱ የሚስብበት ገጽታ ምን እንደሆነ ይብራራ
- አገልግሎቱን ለማቅረብ / ምርቱን ለማምረት የሚያስፈልገው ግብዓትና የማምረቻ ዋጋ
- ምርቱንና አገልግሎቱን የመሸጫ ዋጋ

***የገበያ ዋጋን መተመን***

ኢንተርፕራይዙ የሚያስባቸው ደንበኞች ለመከፈል የሚኖራቸው የገንዘብ መጠን ፍቃደኝነት

ከፍተኛው የገንዘብ መጠን ______________

መካከለኛ  የገንዘብ መጠን ______________

ዝቅተኛው የገንዘብ መጠን ______________

በአካባቢው የሚገኙ  ተወዳዳሪ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ምርታቸውን / አገልግሎታቸውን የሚሸጡበት ዋጋ ምን ያህል ነው?

ኢንተርፕራይዙ የሚያመርተውን / ያለውን ምርት የሚሸጥበት ዋጋስ ምን ያህል ነው?

ከፍተኛው የገንዘብ መጠን ______________

መካከለኛ  የገንዘብ መጠን ______________

ዝቅተኛው የገንዘብ መጠን ______________

ኢንተርፕራይዙ የሽያጩን ዋጋ ለመወሰን ምክንያት የሆነው ምንድነው?

**ኢንተርፕራይዙ የሚጠቀምበት ቦታ/ስፍራን ማቀድ**

- ቢዝነሱ / የንግድ ስራው የሚከናወንበት ስፍራ / ቦታ  (በደንብ ይገለጽ)
- ቦታው የተመረጠበት ምክንያት
- የተመረተው ምርት / ሸቀጥ ለደንበኞች እንዴት ይከፋፈላል ወይም እንዴት ሊደርሳቸው ይችላል?
    - ደንበኞች በቀጥታ ማግኘት ይችላሉ
    - በጅምላ ሻጮችና በችርቻሮ በሚሸጡ ነጋዴዎች በኩል
- ይህንን የመሸጫ / የማከፋፈያ ዘዴ ለመጠቀም የተፈለገበት ምክንያት ምንድነው?

**ገቢያ ለመሳብ / ምርቱን ለማስተዋወቅ ማቀድ**

- ማስታወቂያ በመስራት
- ሽያጭ በማከናወን

**2. የምርት  እቅድ**

- ምርት የሚመረትበት ሂደት ዝርዝር (የሚያስፈልገው ግብዓት፣ የምርት ስራዎቹ ቅደም ተከተል)
- የሚያስፈልገውን ቋሚ እቃ ዝርዝር ከነዋጋው ይገለጽ

| ተራ ቁጥር | የእቃው ዓይነት | ብዛት | ዋጋው |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

**በወር ሊመረት የሚችለው ምርት መጠን ይገለጽ**

**የማምረቻው ቦታና መሳሪያ ይገለጽ**

## ለምርት ተግባር የሚያስፈልጉ ጥሬ እቃዎች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | የሚያስፈልገው የጥሬ እቃ ዝርዝር | ዝርዝር መለያ | መለኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | |
| 2 | | | | | | |
| 3 | | | | | | |
| 4 | | | | | | |
| 5 | | | | | | |

## የሰራተኞች ክፍያ

| ተራ ቁጥር | የስራ መደብ | ሙያ | ወርሀዊ ደመወዝ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| | ጠቅላላ | | | |

## የኢንተርፕራይዙ የስራ ማስኬጃ ወጪዎች


| ተራ ቁጥር | የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ዝርዝር | የገንዘብ መጠን (በወር) |
|---|---|---|
| 1 | የጊዜያዊ ሰራተኛ የጉልበት ዋጋ ክፍያ | |
| 2 | የመብራት ክፍያ (እንዲሁም ውሃ፣ ስልክ እና የመሳሰሉት ወጪዎች) | |
| 3 | የጥገና ወጪ | |
| 4 | የቋሚ እቃዎች የአገልግሎት ዘመን ዋጋ ቅናሽ | |
| | ጠቅላላ | |

**የእያንዳንዱ ምርት የማምረቻ ዋጋ**

- ወርሃዊ የጥሬ እቃዎች ዋጋ
- ወርሀዊ የሰራተኞች ደመወዝ ክፍያ
- ወርሀዊ የስራ ማስኬጃ ወጪ

**3. የአደረጃጀትና የአስተዳደር እቅድ**

- የቢዝነሱ / የንግድ ስራው ዓይነት
- የኢንተርፕራይዙ አወቃቀር




**4. የፋይናንስ (የገንዘብ ፍሰት) እቅድ**

| **የሚያስፈልግ የካፒታል መጠን / የፕሮጀክት ዋጋ** | **የገንዘብ መጠን** |
|---|---|
| ቋሚ እቃ /ንብረት | |
| መሬት | |
| ህንጻ (የማምረቻና የመሸጫ ቦታ) | |
| መሳሪያ | |
| ሌሎች | |
| አጠቃላይ የቋሚ እቃ /ንብረት ዋጋ | |
| ምርት ከማምረት በፊት የሚኖር ወጪ | |
| የመስሪያ ካፒታል /ወርሀዊ የማምረቻ ወጪዎች | |
| - የጥሬ እቃዎች ዋጋ | |
| - የአስተዳደር ወጪዎች | |
| - ወርሀዊ የሰራተኛ ክፍያ | |
| አጠቃላይ የማምረቻ ዋጋ | |
| አጠቃላይ የካፒታል ዋጋ | |

## የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ( ለአምራቾች የቢዝነስ / የንግድ ዘርፍ)
## ዓመታዊ  የትርፍና ኪሳራ ግምት መግለጫ

| ጠቅላላ ሽያጭ | የገንዘብ መጠን |
|---|---|
| (የሚቀነስ) ከሽያጭ ላይ ተመላሽ የሚሆን (ካለ) | |
| የተጣራ ሽያጭ | |
| (የሚቀነስ) የተሸጡ እቃዎች የመጀመሪያ ዋጋ | |
| የተጣራ ትርፍ | |
| (የሚቀነስ) የኦፕሬሽንና የአስተዳደር ወጪ | |
| የማስፈጸሚያ ትርፍ | |
| (የሚቀነስ) የወለድ ወጪ (የብድር ወለድ ክፍያ) | |
| ከታክስ በፊት ያለ ትርፍ | |
| (የሚቀነስ) የገቢ ታክስ ግምት | |
| ከታክስ በኃላ ያለ ትርፍ | |

## የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ( ለአገልግሎት  የቢዝነስ / የንግድ ዘርፍ)
## ዓመታዊ  የትርፍና ኪሳራ ግምት መግለጫ

| ገቢ፡ | የገንዘብ መጠን |
|---|---|
| ሽያጭ | |
| (የሚቀነስ)፡ የኦፕሬሽን ወጪ | |
| የደመወዝ ክፍያ ወጪ | |
| የኪራይ ወጪ | |
| ከሽያጭ ጋር የተያያዘ ወጪ | |
| የወለድ ወጪ (የብድር ወለድ ክፍያ) | |
| ልዩ ልዩ ወጪዎች | |
| ከታክስ በፊት ያለ ትርፍ | |
| (የሚቀነስ) የገቢ ግብር ግምት | |
| ከታክስ በኃላ የተገኘ የተጣራ ወለድ | |

**የገንዘብ ፍሰት**

**ወርሀዊ የገንዘብ ፍሰት ግምት መግለጫ**

| ዝርዝር | ቅድመ ኦፕሬሽን ወቅት | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በወሩ መጀመሪያ ያለ የገንዘብ መጠን | | 10 700 | 20 850 | 37 550 | | | | | | | | | |
| ገቢ የሚሆን ገንዘብ | | | | | | | | | | | | | |
| ከወጪ ቀሪ | 38 700 | | | | | | | | | | | | |
| ብድር | | | | | | | | | | | | | |
| ሽያጭ | | 42 000 | 63 000 | 88 000 | | | | | | | | | |
| የሚሰበሰብ ገንዘብ | | | | | | | | | | | | | |
| ሌሎች ገቢዎች | | | | | | | | | | | | | |
| ጠቅላላ ገቢ የተደረገ ገንዘብ | 38 700 | 52 700 | 83 850 | 125 550 | | | | | | | | | |
| ወጪ | | | | | | | | | | | | | |
| የኦፕሬሽን ወጪ | | 31 850 | 46 300 | 60 750 | | | | | | | | | |
| የቋሚ እቃ ግዢ | 28 000 | | | | | | | | | | | | |
| ታክስ | | | | 11 275 | | | | | | | | | |
| አጠቃላይ የገንዘብ ፍሰት | 28 000 | 31 850 | 46 300 | 72 025 | | | | | | | | | |
| በወሩ መጨረሻ የሚገኝ የገንዘብ መጠን | 10 700 | 20 850 | 37 550 | 53 525 | | | | | | | | | |

**የወጪና ገቢ ሒሳብ መዝገብ**

| ሀብት | የገንዘብ መጠን | እዳ | የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|
| **አሁን ያለ ሀብት** | | **አሁን ያለ እዳ** | |
| በእጅና በባንክ ያለ ገንዘብ | 10 700 | የሚከፈልባቸው ሂሳቦች | |
| የተከፋይ ሂሳቦች | | ታክስ | |
| በእጅ ያለ የጥሬ እቃ ዋጋ | | ሌሎች የሚከፈሉ ሂሳቦች/ወጪዎች | |
| በምርት ላይ ያለ እቃ ዋጋ | | አጠቃላይ ያለ እዳ | |
| ያለቁ ምርቶች ዋጋ | | የረጅም ጊዜ እዳ | |
| ጠቅላላ ሀብት | 10 700 | ብድር | |
| ቋሚ ንብረት | | ጠቅላላ እዳ | |
| ሕንጻ | 10 000 | ከወጪ ቀሪ የሆነ ሂሳብ | |
| መሳሪያ | 18 000 | ካፒታል | 38 700 |
| ጠቅላላ ቋሚ ንብረት | 28 000 | | |
| ጠቅላላ ሀብት/ ንብረት | 38 700 | ጠቅላላ እዳ እና ካፒታል | 38 700 |

**Break-even point**

$$\text{Breakeven Quantity} = \frac{\text{Total fixed cost}}{(\text{price per unit} - \text{variable cost per unit})}$$

$$\text{Breakeven point} = \frac{\text{Total fixed cost} \times \text{price per unit}}{(\text{price per unit} - \text{variable cost per unit})}$$

**(breakeven sales level in dollar terms)**

## Return on investment

$$\text{Rate of return} = \frac{\text{Amount received} - \text{Amount invested}}{\text{Amount invested}} \times 100$$

**Price per unit= Cost per unit + profit (25% of unit cost)**

$$\text{Unit cost} = \frac{\text{Total fixed cost} + \text{Total variable cost}}{\text{Quantity}}$$

**የቢዝነስ እቅድ መቼ ይዘጋጃል?**

- ወደ ቢዝነስ / የንግድ ስራ ለመጀመር ሲታሰብ
- ቢዝነስ / የንግድ ስራ ከመጀመር አስቀድሞ
- ቢዝነሱን / የንግድ ስራውን ለማሳደግ ሲታሰብ
- ቢዝነስ / የንግድ ስራውን በተመለከተ አዲስ ሀሳብ ሲገኝ
- አዲስ ልምድ ሲገኝ

**የቢዝነስ እቅድን ማን ይዘጋጃል/ በማን ይዘጋጃል?**

- በቢዝነሱ / በንግድ ስራው ስራ አስኪያጅ ሊጀመር የታሰበውን የቢዝነስ / የንግድ ስራ ታሳቢ ተደርጎ ይዘጋጃል፡፡
- በዚህ ረገድ ድጋፍ ሰጪ በሆነ አካል እንዲሁም በሂሳብ አዋቂዎች ድጋፍ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡
- የኮምፒውተር ፕሮግራሞችን በመጠቀም እንደ አስፈላጊነቱ ለኢንተርፕራይዙ እንደሚመች በመቀየር መጠቀም ይቻላል፡፡